## ማስታወቂያ

የመንገደኛው የመድረሻ አገር ወይም የመቆምያ ቦታ ጉዞውን ከጀመረበት አገር ውጪ ሲሆን፣ በጉዞው ላይ የዋርሶ ወይም የሞንትሪያል ኮንቬንሽኖች የተባሉት ስምምነቶች ተፈጻሚ ስለሚሆኑና በነዚህ ኮንቬንሺኖች መሰረት በሞት ወይም በአካል ጉዳት እና በእቃ መጥፋት ወይም መበላሸት ምክንያት በመንገደኛው ላይ ለሚደርሰው ጉዳት የአጓገዡ ኃላፊነት አብዛኛውን ጊዜ የተወሰነ ነው። በተጨማሪ "ስለኃላፊነት ወሰን ለኢንተርናሲዮናል መንገደኞች ማስገንዘቢያ" የሚለውንና "ለጉዞ ተጠያቂነት ስላለው ገደብ የተሰጠ ማስታወቂያ" የሚለውን አርእስቶች ይመልከቱ።

## የውል ድርድሮች።

1. በነዚህ ውሎች "ቲኬት" ሲባል እነዚህን የውል ድርድሮችና ማስጠንቀቂያ ጨምሮ ይህን የመንገደኛ ቲኬትና የዕቃ መለያ ቲኬት ወይም የኤሌክትሮኒክ ቲኬት ከተጠቀሙ የመጓጓዣው ደረሰኝ ማለት ነው። "ማጓጓዝ" "የማመላለስ" ተመሳሳይ ነው። "አጓዥ" ሲባል በዚህ ውል መሰረት ግንኙነት ያላቸውን አገልግሎቶች የሚሰጡ የአየር አጓገዦችን ሁሉ ማለት ነው። የኤሌክትሮኒክ ቲኬት ሲባል በአጓገዡ ወይም በወኪሉ የተሰጠ የመጓጓዣ ደረሰኝ ነው። "ዋርሶ ኮንቬንሽን" ሲባል እ.ኤ.አ በጥቅምት 12 ቀን 1929 ዓ.ም. የኢንተርናሲዮናል ማጓጓዝ አንዳንድ ሕግጋቶች ለማዋሃድ በዋርሶ ከተማ የተፈረመውን ስምምነት ወይም ይህን ስምምነት በማሻሻል እ.ኤ.አ. በመስከረም 28 ቀን 1955 ዓ.ም. የተፈረመውን የህግ ፕሮቶኮል አግባብ ያለውን ከሁለት አንዱን ማለት ነው። የሞንትሪያል ኮንቬንሽን ሲባል እ.ኤ.አ. በግንቦት 28 ቀን 1999 ዓ.ም. አንዳንድ የኢንተናሽናል የመጓጓዣ ሕጎችን ለማዋሃድ በሞንትሪያል ከተማ የተፈረመ ውል ማለት ነው።
2. ይህ ማጓጓዝ በኮንቬንሽኑ አገላለጽ መሰረት "የኢንተርናሲዮናል መጓጓዝ" ካልሆነ በስተቀር የዋርሶ ወይም የሞንትሪያል ኮንቬንሽኖች የደነገጉዋቸው ደንቦችና የኃላፊነት ወሰን በዚህ የመጓጓዝ ውል ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ።
3. ከዚህ በላይ ለተነገረው ተቃራኒ ካልሆነ በስቀር (1) በዚህ ቲኬት ውስጥ የተዘረዘሩት ድርድሮች (2) የሚሰራባቸው የዋጋ ማውጫዎች (ታሪፍ) (3) በአጓገዡ ጽህፈት ቤቶች ሁሉ በሚገኙትና የዚህ ውል መሰረት ቃል በሆኑት የአጓገዡ የጉዞ ድርድሮችና ደንቦች ሁሉ በዚህ የማጓጓዣ ውል ወይም እያንዳንዱ አጓዥ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ። ስለሆነም የመጓጓዡ ስራ ከተባበሩት የአሜሪካን ግዛት ወይም ከካናዳ መንግስት ግዛት ውስጥ የሚፈጸም ወይም ከነዚህ ግዛቶች የሚጀመር ሲሆን የነዚህ አገሮች የዋጋ ማውጫ (ታሪፍ) እንደተጠበቁ ይሆናሉ።
4. የአጓገዡ ስም በዚህ ቲኬት ውስጥ በምሕጻረ ቃል ሊጻፍ ይችላል። ሙሉ ስምና ምህጻረ ስሙ በአጓገዡ የዋጋ ማውጫዎች (ታሪፍ) የጉዞ ድርድሮች ደንቦችና ወይም የጊዜ ሰንጠረዦች የተመለከቱት ይሆናሉ። የአጓገዡ አድራሻ በቲኬት ውስጥ መጀመሪያ ከተጻፈው በአጓገዡ ምሕጻረ ስም ፊት ለፊት የተመለከተው የመነሻ አይሮፕላን ጣቢያ ነው። ለመቆሚያ የተስማሙባቸው ቦታዎች በዚህ ቲኬት ውስጥ ወይም በአጓገዡ የጊዜ ሰንጠረዥ የተመለከቱት ናቸው። በዚህ ውል መሰረት ማጓጓዙ የሚፈጸመው በተቀባይ አጓገዦች ሲሆን እንደ አንድ ጉዞ ሆኖ ይቆጠራል።
5. በሌሎች የአየር አጓገዦች መስመር ላይ ለሚፈጸም ማጓጓዝ ቲኬት የሚቆርጥ የአየር አጓዥ ይህን ስራ የሚፈጽመው የነዚህ አጓገ ች ወኪል በመሆን ብቻ ነው።
6. አጓገዡን ከኃላፊነት ነጻ የሚያደርጉ ወይም ኃላፊነቱን የሚወስኑ ሁሉ ለአጓገዡ ወኪሎች አገልጋዮች ወይም እንደራሴዎች እንዲሁም ደግሞ አጓገዡ ለማጓጓዙ ሥራ በሌላ ሰው አይሮፕላን የሚጠቀም ሲሆን ለዚህ ሰው ለወኪሎች ለአገልጋዮች ለእንደራሴዎች ጭምር ተፈጻሚና የጸኑ ይሆናሉ።
7. የተመዘገበ ጓዝ የሚሰጠው የመለያ ቲኬት ላመጣ ሰው ብቻ ነው። ጉዳት ለደረሰበት ጓዝ ተቀባዩ ጉዳት መድረሱን እንዳወቀ ወዲያውኑ ቢበዛ ጓዙን ከተረከበበት ቀን ጀምሮ በ7 ቀን ውስጥ ለአጓገዡ በጽሑፍ ማመልከት አለበት። ጓዝ ዘግይቶ በመድረሱ ምክንያት ለሚደርስ ጉዳት ደግሞ ጓዙን ተቀባይ ከተረከበበት ቀን ጀምሮ ከ21 ቀን በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ጉዳቱን ለአጓገዡ በጽሑፍ ማመልከት አለበት። ማጓጓዙ "ኢንተናሲዮናል ማጓጓዝ" ካልሆነ የአጓገዡን የዋጋ ማውጫዎች (ታሪፍ) ወይም የጉዞ ድርድሮችን ይመልከቱ።
8. በዚህ ቲኬት በአጓገዡ የዋጋ ማውጫዎች የጉዞ ድርድሮች ወይም ተመሳሳይ ደንቦች ውስጥ ተለይቶ ካልተነገረ በቀር ይህ ቲኬት የሚያገለግለው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ብቻ ነው። ዳሩ ግን የዚህ የማጓጓዝ ዋጋ ጉዞው ከመጀመሩ በፊት ሊለወጥ ይቻላል። ተጨማሪ ዋጋ ካልተከፈለ አጓገዡ አይገደድም።
9. አጓገዡ መንገደኞችንና ጓዙን በተቻለ ፍጥነት ለማጓጓዝ የተቻለውን ለማድረግ ይሞክራል። በጊዜ ሰንጠረዥ ወይም በሌላ ዓይነት መንገድ የተሰጡት ሰዓቶች ምንም ዓይነት ዋስትና የሌላቸውና የዚህ ውል መሠረት ቃል አይደሉም። አጓገዡ ያላንዳች ማስታወቂያ ሌላ አጓዥ ወይም አይሮፕላን ሊተካና አስፈላጊ መስሎ ካገኘው በቲኬቱ ውስጥ የተመለከቱትን የማቆሚያ ቦታዎች ሊለውጥ ወይም ሊተው ይችላል የጊዜ ሰሌዳዎችን ያላንዳች ማስ ታወቂያ ለመለወጥ ይችላል። አጓገዡ መንገደኛን ከሌላ አጓዥ ለማገናኘት ምንም ኃላፊነት የለውም።
10. የመንግሥት የጉዞ ደንቦችን መፈጸም ከሀገር መውጫና መግቢያ ፈቃዶችን መያዝና አስፈላጊ ጽሑፎችን ማቅረብ እንዲሁም በተወሰነው ሰዓት ወይም የተወሰነ ሰዓት ከሌለ የሚያስፈልጉትን ሥርዓቶች ለመፈጸም እንዲቻል ቀደም ብሎ አይሮፕላን ጣቢያ መድረስ የመንገደኛው ግዴታ ነው።
11. ማንኛውም የአጓዥ ወኪል ሠራተኛ ወይም እንደራሴ በዚህ ውስጥ የተነገረውን የውል ቃል ለመለወጥ ለመሰረዝ ወይም ለመሻር ሥልጣን አልተሰጠውም።

### ለአገር ውስጥ መንገደኞች ማስታወቂያ

ማጓጓዙ በሙሉ በኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት ውስጥ የሚደረግ ሲሆን ስለ ሞት አደጋ ስለ አካል ጉዳትና ስለ ጠፋ ወይም ጉዳት ስለደረሰበት ጓዝ የአጓገዡ ኃላፊነት በኢትዮጵያ የንግድ ሕግ መሠረት የተወሰነ ነው።

በታሪፍ ደንቦች መሠረት የተሸጠ።
የዚህ ቲኬት ዋጋ ጉዞው ከመጀመሩ በፊት ሊለወጥ ይችላል
የኢትዮጵያ አየር መንገድ አ.ማ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

## ለኢንተርናሽናል መንገደኞች ስለ ኃላፊነት ወሰን የተሰጠ ማስገንዘቢያ።

የመድረሻ ወይም የሚቆሙበት ቦታ ከተነሱበት አገር ውጪ የሆነ ጉዞ የሚጀምሩ መንገደኞች ጠቅላላ ጉዞአቸውና በመነሻ ወይም በመድረሻ አገር በከፊል የሚደረገውን ጉዞ ጨምሮ የዋርሶ ኮንቬንሽን ወይም የሞንትሪያል ኮንቬንሽን የተባለው ስምምነት የሚፈጸም መሆኑን እንዲያውቁት ይለመናሉ። ጉዞው ወደ ተባበሩት የአሜሪካን መንግሥት ግዛት ወይም ከዚህ ግዛት የሚጀመር ወይም መቆሚያ ቦታው በዚህ ግዛት ውስጥ ሲሆን በዋርሶው ወይም በሞንትሪያል ኮንቬንሽንና በልዩ ውሎች መሠረት መንገደኛው ላይ ለሚደርሰው የሞት ወይም የአካል ጉዳት አንዳንድ ይህን ውል የፈረሙ አጓጓዦች ኃላፊነት አብዛኛውን ጊዜ ከ75,000 የአሜሪካን ዶላር አይበልጥም። ለዚህ ለተወሰነ ኃላፊነት አጓገፉ ጥፋተኛ ለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ አያስፈልግም።
መንገደኞችን የሚያጓጉዘው ይህን ልዩ ውል ያልፈረመ አጓዥ ሲሆን ወይም ጉዞው በተባበሩት የአሜሪካን መንግሥት ግዛት ውስጥ የማይደረግ ወይም በዚህ ግዛት ውስጥ መቆሚያ ቦታ የሌለ ሲሆን በመንገደኞች ላይ ለሚደርሰው የሞት ወይም የአካል ጉዳት የአጓገፉ ኃላፊነት ወሰን አብዛኛውን ጊዜ ከ10,000 ወይም 20,000 የአሜሪካን ዶላር አይበልጥም።

በማንኛውም የቲኬት መሸጫ ቦታ ይህን ልዩ ውል የፈረሙ አጓዦች ስም ዝርዝር ስለሚገኝ መንገደኞች ለመመልከት ይችላሉ።
ተጨማሪ ዋስትና ቢፈለግ ከግል ኩባንያዎች ኢንሹራንስ መግዛት ይቻላል። ይህ ኢንሹራንስ በዋርሶ ኮንቬንሽን፣ በሞንትሪያል ኮንቬንሽን ወይም በልዩ የጉዞ ውሎች ከተወሰነው የአጓገፉ  ኃላፊነት ጋር ተቃራኒ አይሆንም። ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልግ የአየር መንገዳችሁን ወይም የኢንሹራንስ ወኪሎችን ጠይቁ።

ማሳሰቢያ፡ ከላይ የተነገረው የ75,000 የአሜሪካን ዶላር  ኃላፊነት ወሰን የዳኝነትና ተመሳሳይ ወጪዎችን ይጨምራል። ነገር ግን ክሱ የቀረበው የዳኝነትና ተመሳሳይ ወጪዎች በተለይ ለብቻ እንዲከፈሉ ሕግ በሚያስገድድበት ጊዜ የኃላፊነቱ ወሰን ከ58,000 የአሜሪካን ዶላር አይበልጥም ይህም የሚሆነው የተባሉትን የዳኝነትና ተመሳሳይ ወጪዎችን ሳይጨምር ነው።

## ለጉዞ ተጠያቂነት ስላለው ገደብ የተሰጠ ማስታወቂያ።

ዕቃው ከፍ ያለ ዋጋ ያለው መሆኑ በቅድሚያ ተገልጾ ተገቢው ተጨማሪ ክፍያ ካልተደረገ በቀር አጓገፉ ለጠፋ፡ ለዘገየ ወይም ለተበላሸ ዕቃ ሊያደርግ የሚችለው ክፍያ መጠን የተወሰነ ነው። ለአብዛኛው ዓለም አቀፍ ጉዞ /በአንድ አገር ክልል ውስጥ የሚከናወኑ የዓለም አቀፍ በረራ ክፍል የሆኑ ጉዞዎችን በመጨመር/ አጓገፉ በኃላፊነት ለተቀበለው ዕቃ የሚኖረው ተጠያቂነት ለአንድ ፓውንድ ክብደት እስከ 9.07 የአሜሪካ ዶላር ሊደርስ የሚችል ሲሆን /በኪሎ 20 የአሜሪካን ዶላር/ አጓገፉ በኃላፊነት ላልተቀበለው ዕቃ የሚኖረው ተጠያቂነት በመንገደኛ ከ400 የአሜሪካን ዶላር ሊበልጥ አይችልም። የሞንትሪያል ኮንቬንሽን ተፈፃሚ በሚሆንበት ጊዜ የአጓገፉ ተጠያቂነት አግባብ ባላቸው የኮንቬንሽኑ አንቀጾች መሰረት ይሆናል።
ጉዞው በሙሉ የሚከናወነው በዩናይትድ እስቴትስ የግዛት ክልል ውስጥ ብቻ የሆነ እንደሆነ በአገሩ ሕግ መሠረት አጓገፉ ለዕቃ የሚኖረው ተጠያቂነት ከፍተኛ መጠን በመንገደኛ ቢያንስ 2,800 የአሜሪካን ዶላር ይሆናል። በተወሰኑ ዕቃዎች ዋጋ ላይ ተጨማሪ ተመን ሊሰጥባቸው የሚቻል ሲሆን አንዳንድ አጓዦች ውድ፡ ተሰባሪ ወይም ጠፊ ለሆኑ ዕቃዎች ማናቸውንም ኃላፊነት አይቀበሉም። ተጨማሪ መረጃ ቢያስፈልግ ከአጓገፉ ለማግኘት ይቻላል።

For all International Carriage to which the Warsaw Convention or the Montreal Convention applies, in any action brought before an Italian Court, the limit of Liability shall be One hundred thousand (100,000) special drawing rights as defined by the International monetary Fund, to be converted into the national currency in accordance with the method of valuation applied by the international monetary fund.

---

የዋርሶ ኮንቬንሽን ወይም የሞንትሪያል ኮንቬንሽን ተፈጻሚ በሚሆንበት ከማናቸውም ኢንተርናሽናል የአየር ጉዞ በተገናኘ በኢጣሊያን ፍርድ ቤቶች ክርክር ቢነሳ የአጓዡ የኃላፊነት ጣሪያ መጠን ከአንድ መቶ ሺ /100,000/ ስፔሻል ድሮዊንግ ራይት የማይበልጥ ሲሆን ይህም የኢንተርናሽናል የገንዘብ ተቋም በሚጠቀምበት የምንዛሪ ደንብ መሠረት ወደአገሩ ገንዘብ ተመንዝሮ ይታሰባል።

## Airport Check-In Requirements

Please make sure that you are in possession of all required travel documents with the appropriate entry visas, including a vaccination certificate.

Please indicate your seat and special meal preference at the time of booking your flight.

All ETHIOPIAN flights are smoke free.

## በኤርፖርት ከተሳፋሪዎች የሚጠበቁ ግዴታዎች

እባክዎ ለጉዞ የሚያስፈልጉ ሰነዶችን ማለት የሚሄዱበት አገር የመግቢያ ቪዛ የክትባት ሠርተፊኬትና የመሳሰሉትን አሟልተው መያዞን ያረጋግጡ። ለተሟላ መስተንግዶ እባክዎን በረራውን በሚያስመዘግቡበት ጊዜ የመቀመጫ ቦታና የምግብ ምርጫዎን ያስታውቁ።

በሁሉም የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራዎች ላይ ማጨስ የተከለከለ ነው።